የሰበር መ/ቁ. 29780

ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/5 መሰረት በበታች ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን አመልካቾች በተጠሪ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 9 ቀበሌ 07 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 1288 የሆነውን ቤት በውርስ ያገኙት መሆኑን ገልፀው ይህንኑ ቤት ቀልፈን እንደሄድን ተከሳሽ በሀይል በመክፈት ስለገቡበት እንዲያስረክቡንና ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሱት ክርክር ከሳሾች በመ.ቁ. 02330 በዚሁ ቤት የሁከት ይወገድልን ክስ መስርተው ፍ/ቤቱም ውሣኔ የሰጠ ስለሆነ በተመሳሳይ ጉዳይ ድጋሚ ክስ



መቅረቡ በአግባቡ ስላልሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ ተከሳሽ በዚህ ጉዳይ አስቀድሞ ውሣኔ መስጠቱን ለማስረዳት ያቀረቡትን የፍ/ቤት ውሣኔ ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው ከሳሾች ወራሽነታቸውን ገልፀው ተከሳሽ ቤቱን ትልቀቅልን በማለት ክስ መስርተው ፍ/ቤቱም ውሣኔውን ሲሰጥ ይህንኑ ጭብጥ በመከተል ተከሳሿ ቤቱን በይዞታነት የምትጠቀምበት መሆኗን ከቀበሌው አረጋግጦ ከሳሾች እንደ ክሳቸው ባለማስረዳታቸው ጥያቄያቸውን ባለመቀበል መዝገቡን እንደዘጋ መረዳት የተቻለ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/5 መሠረት በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነና ፍርድ የተሰጠበት ከሆነ ተከራካሪ ወገኖች ድጋሚ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ ስለተደነገገ ከሳሾችም በዚህ መዝገብ ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ክሱን በብይን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች በድጋሚ ያቀረቡት አቤቱታ አስቀድሞ ውሣኔ ያገኘ ስለመሆኑ ተጠሪ ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ከላይ እንደተጠቀሰው ጉዳዩ አስቀድሞ ውሣኔ ያገኘ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመ/ቁ. 02330 አመልካቾች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት በወረዳ 9 ቀበሌ 07 ክልል ከወላጆቻችን በውርስ ያገኘነውና በይዞታችን አድርገን

የምንጠቀምበት የቤት ቁጥር 1288 የሆነውን ቤታችንን በቁልፍ ቆልፈነው እንዳለ እንዳንገባ፣ እንዳንወጣና እንዳንገለገልበት በማድረግ ተከሳሽ ሁከት የፈጠረችብን ስለሆነ ሁከቱ እንዲወገድና ቤታችንን ለቃ እንድትወጣ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነው መዝገቡ ላይ ያቀረቡት ክስ ደግሞ ከላይ እንደተመለከተው ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪ ቁልፉን ከፍተው በመግባት በኃይል የያዙት ስለሆነ ያስረክቡን በማለት ነው፡፡

በሁለቱም መዝገቦች ላይ አመልካቾች የጠየቁት ዳኝነት /Relief/ አቤቱታ የቀረበበትን ቤት ለመረከብ ቢሆንም በአቤቱታቸው ላይ የጠቀሱት ዝርዝር ፍሬ ነገር ሲታይ ግን በመጀመሪያው መዝገብ የተፈጠረው ሁከት ተወግዶ ቤቱን እንረከብ በማለት የጠየቁ እንደመሆኑ ሁከት አለ የለም የሚለው ነጥብ በጭብጥ ተይዞ የሚፈታ ሲሆን በሌላ በኩልም በሁለተኛው መዝገብ ባቀረቡት አቤቱታ ቤቱ ያለአግባብ የተወሰደባቸው መሆኑን በመግለጽ እንዲመለስላቸው የጠየቁ በመሆኑ በዚህ መዝገብ በጭብጥ ሊያዝ የሚችለው ፍሬ ነገር ሁከት አለ ወይንስ የለም የሚል ሳይሆን ባለቤትነት የመፋለም ክስን /petitory action/ የሚመለከት በመሆኑ በጭብጥም ተይዞ የሚፈታው ፍሬ ነገር ይሄው ባለቤትነትን አስመልክቶ የቀረበው ክስ ስለሚሆን በሁለቱ መዝገቦች ላይ የቀረበው ክርክር በጭብጥ የተለያየ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች አስቀድሞ ውሣኔ ባገኘ ጭብጥ ላይ ድጋሚ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት ሁለተኛውን ክስ ሳይቀበሉ መቅረታቸው የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06644 ኅዳር 8 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26636 በመጋቢት 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06644 በተጠሪ ላይ ያቀረቡት አቤቱታ አስቀድሞ በመ.ቁ. 02330 ውሣኔ ካረፈበት የተለየ በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ያደረጉትን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 341 መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ